# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
# ሪፐብሊክ መንግሥት
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
## በአርብቶአደር የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት
## ላይ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት
## ሪፖርት

**ሰኔ 2003 ዓ.ም**

## ማውጫ

ክፍል አንድ ........ 1
**1.1 መግቢያ** ........ 1
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ........ 2
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ........ 2
ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የፌዴራል እገዛ ቦርድ ........ 4
የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት ........ 5
የሰው ሃይል ........ 5
የፋይናንስ ምንጭ ........ 5
የኦዲቱ አላማ ........ 6
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ/ጭብጥ/ ........ 6
የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ ........ 7
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴዎች ........ 7
**1.2 የአሰራር ሂደት መግለጫ** (Process Description) ........ 8
የተመጣጣኝ ልማት ዳይሬክቶሬት በልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ያለው የስራ ሂደት፡- ........ 8
የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት፡- ........ 8
ክፍል ሁለት ---------------------------------------- 9
ግኝቶች/Findings/ ........ 9
በአርብቶአደሩ አካባቢ የእንስሳት መኖ አቅርቦት ከፍላጐት ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ፡- ........ 9
የመኖ ባንኮች በአርብቶአደሩ አካባቢ መቋቋማቸውን በተመለከተ፡- ........ 11
የተሻሻለ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም ስልት/ ሥርዓት ስለመኖሩ፡- ........ 12
በአርብቶአደሩ አካባቢ ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን ንፁህ የመጠጥ ውሃ ስለመኖሩ፡- ........ 14
የተሻሻሉ የዳልጋ ከብት ዝርያዎችን ማራባትና ማሰራጨትን በተመለከተ፡- ........ 17
በአርብቶ አደር ወረዳዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚደረገው የጤና አገልግሎትን በተመለከተ፡- 18
ለአርብቶአደሩ ከዳልጋ ከብት ምርትና ምርታማነት ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በተመለከተ፡- ........ 21
በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎች የሚጠናከሩበት ሥርዓት ስለመኖሩ፡- ........ 22
በአርብቶአደሩ አካባቢ የዳልጋ ከብት ልማትን የሚደረገውን እገዛ በተመለከተ፡- ........ 23
ክፍል ሶስት ........ 25
መደምደሚያ (Conclusions) ........ 25
ክፍል አራት ........ 28
የማሻሻያ ሀሳቦች/Recommendation/ ........ 28

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

1. በኢትዮጵያ አርብቶ አደር አካባቢዎች ብዙ የዳልጋ ከብቶች እንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: መረጃዎቹም በኦሮሚያ ክልል 4,339,638.00፣ በሱማሌ ክልል 3,796,000.00፣ በአፋር ክልል 2,336,488.00 እና በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ 1,556,273.00 በድምሩ 12,028,399.00 የሚገኙ መሆኑን ያሳያሉ:: ይህም ሀገሪቱ ካላት አጠቃላይ የዳልጋ ከብት ብዛት 24.39 በመቶኛውን የሚሸፍን ነው::
2. ከዚህም በተጨማሪ የአርብቶአደር አካባቢ በተደጋጋሚ ድርቅና በሌሎች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ሰለባ ከመሆኑም በላይ የአርብቶአደሩ ማህበረሰብ ከድህነቱ መባባስ ጋር ተያይዞ የሚደርስበትን አደጋ ተሸክሞ የሚጓዝበት አቅም በማጣቱ ልማዳዊ አካባቢን የመጠቀም ዕውቀቱን በመጠቀም ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ህይወቱን በማቆየት ኑሮውን ሲገፉ ይታያል::
3. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 256/94 የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀትን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ መሠረት የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ለመጀመሪያ ጊዜ በ1994 ዓ.ም ተቋቋመ:: ከዚያም በ1998 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 471/98 የአስፈፃሚ አካላትን ለማሻሻል በወጣው የማቋቋሚያ አዋጅ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አንዱ ነበር:: እንደዚሁም በ2001 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 641/2001 የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮች መካከል እርስ በእርስ መከባበር፣ መቻቻልና መተማመን፣ ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን ለማድረግ ግጭትን ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው ከማንኛውም አካላት ጋር ተባብሮ እንዲሰራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል::
4. ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች/ሱማሌ፤ አፋር፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ/ በፌዴራል መንግሥት የሚደረገውን ልዩ ድጋፍ በተቀናጀና ስርዓት ባለው መልክ ለመፈጸም እንዲቻል ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 471/98 ከተሰጠው ተልዕኮ በተጨማሪ የተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በአባልነት ያካተተ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል የልዩ እገዛ ቦርድ ማቋቋም በማስፈለጉ በደንብ ቁጥር 103/96 እና በተሻሻለ ደንብ ቁጥር 128/99 ቦርዱ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን የአጎራባች ክልሎች ድጋፍ ውጤታማ እንዲሆን የማስተባበርና የማቀናጀት ተልዕኮ በዚሁ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተሰጥቶታል::

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

5. በሀገራችን ዘላቂ ሠላም የተጠናከረ የመንግስታት ግንኙነትና የተመጣጠነ ልማት በ2012 እውን ሆኖ ማየት የሚል ነው፡፡

### ተልዕኮ

6. የፌዴራል አካላት እገዛን በማስተባበርና በማቀናጀት ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ተመጣጣኝ ልማት ማረጋገጥ፣ የግጭት መከላከልና አፈታት ስርዓት በመዘርጋት እና በተለያዩ ሃይማኖትና እምነት ተከታዮች መካከል ያለውን መልካም ግንኙነቶች በማዳበር የሕዝቡን ሠላም ማረጋገጥ እንዲሁም የፌዴራል ክልል ግንኙነቶች ማዕከል ሆኖ በማገልገል የፌዴራል ሥርዓቱን ማጠናከር ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

በአዋጅ ቁጥር 471/98 የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት፡-

- የሕዝቡ ሰላም መጠበቁን በማረጋገጥ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 እና 62/6 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣
- አግባብነት ያላቸው ሕጐች እንደተጠበቁ ሆነው፤ በክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን ፖለቲካዊ መፍትሄ ያቀርባል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈፃፀሙን ያስተባብራል፣
- ለክልሎች በተለይም ለታዳጊ ክልሎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌዴራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣
- ሌሎች የፌዴራል መንግሥት አካላት ለታዳጊ ክልሎች የሚያደርጓቸውን ድጋፎችን ያስተባብራል ያቀናጃል፣
- በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል እርስ በርስ መከባበር፤ ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን በማድረግና ግጭትን ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው ከሌሎች ከማናቸውም አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፣

- *የፌዴራል ፖሊስ፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶችና ፈንጂ የማምከን ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ማረጋገጥ፣*

*የሚሉት ናቸው::*

7. *ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአርብቶአደሩን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማቃለልና የልማት ተቋዳሽ ለማድረግ መንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቀየስ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል:: የዚሁ ጥረት አካል የሆነውን የአርብቶአደሩ ማህበረሰብ የልማት ኘሮጀክት*(PCDP) *በመቅረፅ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል::*
8. *የልማት ኘሮጀክቱ በ15 ዓመታት /እ.ኤ.አ. ከ2003-2018 ዓ.ም/ ጊዜ ውስጥ የሚተገበር ሲሆን በሶስት የ5 ዓመታት ምዕራፎች በመክፈል ነው የተቀረፀው:: በኘሮጀክቱ በሶስተኛው ምዕራፍ ማብቂያ /እ.ኤ.አ በ2018 ዓ.ም/ የአርብቶአደሩ አካባቢዎችን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የማህበራዊ ግልጋሎቶች ሰፍነው ህብረተሰቡና የአካባቢው መስተዳድር ከማናቸውም አደጋ ራሳቸው የሚቋቋሙበትና ፈጣን ምላሽ የመስጠት አቅም ገንብተው በሀገሪቷና በራሳቸው የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ተዋናይ ሆነው የሚታዩበትን ግብና ዓላማ የያዘ ነው::*
9. *በመጀመሪያው ምዕራፍ በ32 ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 516 ቀበሌዎች ላይ የልማት ስራ የተሰራና የተጠናቀቀ ሲሆን አንዳንድ ተጀምረው ያልተጠናቀቁትን በሁለተኛው ምዕራፍ ተጠናቀዋል:: የሁለተኛው ምዕራፍ በ55 ወረዳዎች ላይ የሚተገበርና ከተጀመረ ሁለት ዓመታት ያስቆጠረ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሊሰሩ የታቀዱ አራት ዋና ዋና ዘርፎችን እንዲይዝ ተደርጓል::*
10. *እነዚህም አንደኛ ኑሮን በዘላቂነት የማሻሻል ዘርፍ ሲሆን ይህ ማህበረሰቡን በዘላቂ ኑሮ የማጠናከር ስራ የሚሰራበት ነው:: ሁለተኛ የአርብቶአደር አካባቢ አደጋ መከላከልና አስተዳደር ሲሆን ይህም ድርቅ፤ ጐርፍ የመሳሰሉት ከመከሰታቸው በፊት የቅድሚያ ዝግጅት ስራ የሚሰራበት ነው:: ሶሥተኛ ተሣትፎአዊና ድርጊታዊ የመማርና ዕውቀት ማኔጅመንት ሲሆን አራተኛ የኘሮጀክት ሥራ አመራርና ማስተባበር ናቸው::*
11. *ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ ሰላምና፣ ፀጥታ ለማስፈን ግጭቶችን መፍታትና መከላከል፣ እንደዚሁም በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነት ለማስፈን የፌዴራል ሥርዓቱ እንዲጠናከርና ፌዴራሊዝም እንዲጐለብት ለማድረግ በመሰረታዊ አሠራር ለውጥ ጥናት መሠረት መ/ቤቱ ከግንቦት 2001 ዓ.ም ጀምሮ ድርጅታዊ አወቃቀሩን በአዲስ መልክ ቀርጿል::*

## ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች የፌዴራል እገዛ ቦርድ

### የቦርዱ ዓላማ

- የፌዴራል መንግሥቱ አካላት በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች የሚሰጡትን ድጋፍ ማቀናጀት፣
- ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ፈጣንና ተመጣጣኝ ልማት ለማስገኘት የማስፈፀም አቅም ግንባታ፤ የመልካም አስተዳደርና ልማት ለማፋጠን ልዩ ድጋፍ ለመስጠት

### የቦርዱ ኃላፊነትና ተግባር

- የክልሎችን የአቅም፤ የልማት፤ የመልካም አስተዳደር ክፍተትን ይለያል፤ ዕቅድን ከክልሎች ጋር በመተባበር በጋራ ያዘጋጃል፤ ያቀናጃል ተግባራዊም ያደርጋል
- ራሳቸውን የሚያስችል ቀጣይ የአቅም ግንባታ ለክልሎች ያደርጋል
- በልማትና በመልካም አስተዳደር ለክልሎች የሚደረገውን የፌዴራል መ/ቤቶችን ዕገዛ ያቀናጃል

12. ቦርዱ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራና 10 የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችን አባል ያደረገ ሲሆን እነሱም:-
    - የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
    - የግብርና ሚኒስቴር
    - ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
    - ትምህርት ሚኒስቴር
    - የውሃ እና ኢነርጂ ልማት ሚኒስቴር
    - ሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር
    - ሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር
    - የሴቶች፣ የወጣቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር
    - ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
    - የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ኤጀንሲ

    ናቸው::

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት

13. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአንድ ሚኒስትርና በአንድ ሚኒስትር ዴኤታ የሚመራ ሲሆን አራት ወሳኝ የሥራ ሒደቶች /በተቀናጀ ልዩ ድጋፍ ተመጣጣኝ ልማት የማረጋገጥ ወሳኝ የሥራ ሒደት፤ የግጭት መከላከልና አፈታት ወሳኝ የሥራ ሂደት፤ የመንግሥታት ግንኙነቶችን የማጠናከር ወሳኝ የሥራ ሂደት፤ የሃይማኖትና እምነት ጉዳዮች ወሳኝ የሥራ ሂደት/ እና ለሚኒስትር ዴኤታው ስድስት ደጋፊ የሥራ ሒደቶች አሉት::

    ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሩ ሲሆን ወሳኝ የሥራ ሂደቶች ተጠሪነታቸው ለሚኒስትር ዴኤታ ነው::

14. የአርብቶአደር ማህበረሰብ ልማት ኘሮጀክት በፌዴራል፤ በክልልና በወረዳ ደረጃ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የተደራጀና አፈፃፀሙም ባሉት የመንግሥት መ/ቤቶች የስልጣን ተዋረድ መሰረት ሲሆን ተጠሪነቱም ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ ነው::

## የሰው ሃይል

15. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በአጠቃላይ 326 ቋሚ ሠራተኞች ሲኖሩት ከዚህ ውስጥ 237 ወንዶች እና 89ኙ ሴቶች ናቸው:: በስሩ የሚተዳደረው የአርብቶአደር ማህበረሰብ ልማት ኘሮጀክት ደግሞ 22 ሠራተኞች ሲኖሩት 16 ወንዶች እና 6ት ሴቶች ናቸው::

## የፋይናንስ ምንጭ

16. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መንግስት በሚመድብለት በጀት የሚተዳደር ሲሆን ይኸውም:-

    - በ2001 በጀት ዓመት 10,395,1743 የተመደበ ሲሆን ከዚሁ ዉስጥ ብር 8,488,399 ወጪ ሲሆን፣
    - በ2002 በጀት ዓመት ደግሞ 13,855,800 የተመደበና ከዚሁ ዉስጥ ብር 12,117,815 ወጪ ሆኗል::

17. የአርብቶአደር ማህበረሰብ ልማት ኘሮጀክት የበጀት ምንጭ ከአለም ባንክ የተገኘ ብድርና ዕርዳታ፣ ከአለም አቀፍ ግብርና ልማት ፈንድ የተገኘ ብድርና ዕርዳታ፣ የተጠቃሚው ክልል መንግሥታት መዋጮና የማህበረሰብ አስተዋፅኦ በገንዘብ፤ በጉልበትና በአካባቢ ጥሬ ዕቃ እንዲሁም ከመንግስት ከሚሰበሰብ በጀት የሚንቀሳቀስ ሲሆን ኘሮጀክቱም በሶስት ምዕራፍ የተከፈለ ነው:: ለመጀመሪያው ምዕራፍ /እ.ኤ.አ.

ከ2003-2008 ዓ.ም/ 60 ሚሊዮን ዶላር የተመደበ ሲሆን ለሁለተኛው ምዕራፍ /እ.ኤ.አ. ከ2008-2013 ዓ.ም/ 138.3 ሚሊዮን ዶላር ተመድቦለታል፡፡

## <u>የኦዲቱ አላማ</u>

18. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በአርብቶአደሩ ዘንድ በዳልጋ ከብት ሃብት ልማት ላይ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በመመርመር ብቃት ባለው መንገድ የሚከናወኑና ወጪውም ቁጠባን ያገናዘበና አላማውንም ስኬታማ ማድረጉን በማጣራት የአሰራር ችግሮች ካሉ ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን (Recommendations) ለመስጠት ነው፡፡

## <u>የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ/ጭብጥ/</u>

**19.** በአርብቶአደር የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ላይ ሊከናወን ለታቀደው የክዋኔ ኦዲት አንድ የኦዲት ጭብጥ (Issue) ተለይቷል እሱም፡-

1. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ለአርብቶ አደሩ የሚያደርገውን ልዩ ድጋፍና ሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ለአርብቶ አደሩ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚያከናውኑት የመኖ እና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፤ የጤና አጠባበቅ፤ ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴዎች፤ ምርታማነት እና በመጠን የማሳደግ እንዲሁም የግንዛቤ ማዳበርና የመረጃ አያያዝ ተግባራትን የማስተባበርና የማቀናጀት ሥራው ብቃት ባለው መንገድ የሚከናወኑና ስኬታማ መሆናቸውን ማጣራት፤

   የሚል ሲሆን በ4 ንዑስ የኦዲት ጭብጦች ተከፍለዋል፡፡

   **1.1.** የአርብቶ አደሩን የዳልጋ ከብት ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የመኖ፤ ግጦሽ መሬትና ውሃ አቅርቦት፤ የዝርያ ማሻሻል ተግባራት በብቃት የሚከናወኑ እና ስኬታማ መሆናቸውን ማጣራት፤

   **1.2.** በአርብቶ አደሩ አካባቢ የዳልጋ ከብቶች የግጦሽ አካባቢና መኖሪያ ስፍራ ጤናማ የማድረግ ስራ የሚከናወን፤ የሕክምና አገልግሎት እና የመድሐኒት አቅርቦት የተሟላ መሆኑን ማጣራት፤

   **1.3.** የዳልጋ ከብቶች ምርታማነትና ብዛትን ለመከታተል የሚያስችል የክትትልና የመረጃ አያያዝ ሥርዐት መዘርጋቱን፣ ለአርብቶአደሩ ሕብረተሰብ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና የሚሰጥበት ስርዓት መኖሩንና ተፈፃሚ መደረጉን እና ለአርብቶ አደሩ የሚደረገው ልዩ ድጋፍ የአርብቶ አደሩን መሰረታዊ ፍላጎት ያሟላ መሆኑን በተመለከተ፡-

   **1.4.** በአርብቶ አደሩ የዳልጋ ከብት ሐብት ልማት ዙሪያ ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴዎችን ለአርብቶ አደሩ ለማድረስ የሚያስችል ስርዐት ስለመዘርጋቱና ስኬታማ ስለመሆኑ ማጣራት፤

## <u>የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/</u>

**20.** ለተመረጠው የኦዲት አቅጣጫ/ጭብጥ/ 27 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ በቅድሚያ አስተያየት እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለሚመለከተው የፌዴራል ጉዳዮች ኃላፊዎች ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

## <u>የኦዲቱ ወሰንና ዘዴዎች</u>

**21.** ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2001-2002 በጀት ዓመት የነበረውን የአርብቶአደር የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲሆን በአርብቶአደር ዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዙሪያ ድጋፍ የሚሰጡ የሴክተር መስሪያ ቤቶችን ማለትም ግብርና ሚኒስቴር/ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት/፣ የኦሮሚያ አርብቶአደር ኮሚሽን፤ የአርብቶአደር ማህበረሰብ ልማት ኘሮጀክት ማስተባበሪያ፤ የሱማሌና የአፋር አርብቶአደር ቢሮዎች እና በተመረጡ የአርብቶ አደር ወረዳዎች መረጃዎች በመከለስ፤ ቃለ መጠይቅ በማቅረብና የመስክ ጉብኝት በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 1.2 የአሰራር ሂደት መግለጫ (Process Description)

### የተመጣጣኝ ልማት ዳይሬክቶሬት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ያለው

### የስራ ሂደት:-

በክልሎቹ ያሉትን የተለያዩ የአቅም ክፍተቶች/Gaps/ እንዲጠኑ ያስተባብራል ይመራል

በድጋፍ ጉዳዮቹ እንዲለዩ ከቢ.ጋር ዝግጅት ጀምሮ መረጃ ይሰበስባል

የተሰበሰቡትን መረጃዎች ይተነትናል ለመነሻ ሰነድም እንዲዘጋጅ ያደርጋ

የጥናት ሥርዓቱ ከአጋር ድርጅቶች ጋር እንዲጠና ያደርጋል

አዳዳዲስ ተሞክሮዎችን ያበረታታል ያስፋፋል

ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች/ እንዲቀረፁና ለባለ ድርሻ አካላት እንዲከፋፈሉና እንዲፈፀሙ

በበላይነት ይመራል

### የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት:-

ከአርብቶ አደሩ የድጋፍ ጥያቄ ይቀርባል

**የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች በጉዳዩ ላይ ህዝቡን ያወያያሉ**

**የፕሮጀክት ቅደም ተከተሎች ይዘጋጃሉ**

**ፕሮጀክቱ የፈንድ አቅርቦት ያዘጋጃል**

**ፕሮጀክቱ ይሰራል**

**ለተጠቃሚው አካል ይተላለፋል**

**የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ፕሮጀክቶቹን በበላይነት ይመራል**

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች/Findings/

**2.1 የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ለአርብቶ አደሩ የሚያደርገውን ልዩ ድጋፍና ሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ለአርብቶ አደሩ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚያከናውኑት የመኖ እና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴዎች፣ ምርታማነት እና በመጠን የማሳደግ እንዲሁም የግንዛቤ ማዳበርና የመረጃ አያያዝ ተግባራትን የማስተባበርና የማቀናጀት ሥራው ብቃት ባለው መንገድ የሚከናወኑና ስኬታማ መሆናቸውን በተመለከተ:-**

**በአርብቶአደሩ አካባቢ የእንስሳት መኖ አቅርቦት ከፍላጐት ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ:-**

**22.** የአርብቶአደሩ የዳልጋ ከብት አመጋገብ ለማሻሻል የመኖ አዘገጃጀትና አቅርቦት የሚያድግበት ሁኔታ ሊመቻችና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተለይም አርብቶአደሩ ዓመቱን ሙሉ በአካባቢው ሊገኙ የሚችሉ የመኖ አይነቶችን ለይቶ በማወቅ ያለውን መኖ አመጣጥኖ ለመመገብ እንዲችል ግንዛቤ የሚያገኝበት ሥርዓት እንዲዘረጋ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የግብርና ሚኒስቴርን በማስተባበርና ስለ ተፈፃሚነቱም ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

**23.** በአርብቶአደሩ አካባቢ በናሙና ጉብኝት ባደረግንባቸው የኦሮሚያ እና የሶማሌ ክልል አርብቶአደር ወረዳዎች ለማየት የተቻለው ለከብቶቻቸው በመኖነት የሚጠቀሙት ከሰብል ተረፈ ምርት፣ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮችን ዘርቶ በማምረት፣ ሞላሰስ እና የግጦሽ መሬት ናቸው፡፡ በአካባቢው በበጋ ወቅት ከፍተኛ የሆነ የመኖ እጥረት ችግር እንዳለ ታውቋል፡፡ በአንዳንድ ወረዳዎች ያለው የከብት ብዛትና የመኖ ሁኔታ/አቅርቦት አይጣጣምም፡፡

**24.** ይህንን በማስመልከት በኦሮሚያ ክልል ፈንታሌና ሚኤሶ ወረዳ፣ በሱማሌ ክልል ጅጅጋ፣ ቀብሪበያ፣ ጉርሱም እና አቡበሬ ወረዳዎች፣ በአፋር ክልል ገዋኔ፣ ሚሌ፣ እና አፋምቦ ወረዳዎች ባደረግነው ቃለ መጠይቅ የመኖ መጠኑ በወረዳው ካሉት የከብት ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ እንዳልሆነ የገለፁ ሲሆን በአፋር ክልል ዱኙቲና አይሳይታ ወረዳ የሚጣጣም መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህም ማለት ጉብኝት

ከተደረገባቸው 11 ወረዳዎች ውስጥ በ9ኙ /82%/ እጥረት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

**25.** በዚህ ጉዳይ ያነጋገርናቸው ወረዳዎች የእንስሳት፣ ሰብል እና ግብርና ጽ/ቤቶች ተጠይቀው በአካባቢው በተደጋጋሚ በዝናብ እጥረት እና በድርቅ የሚመታ በመሆኑ፤ የግጦሽ መሬቱም በፊት ከነበረው መሬት ለእርሻና ለሌሎች አገልግሎቶች እንዲውል መደረጉ፤ የነበረውም የግጦሽ መሬት በፊት ከነበረው 50% የሚሆነው በአላስፈላጊና ለመኖነት በማያገለግሉ አረሞች በመወረሩ እንዲሁም ያለው ለመኖነት የሚውሉ ግብዓቶች አቅርቦት በወረዳው ካለው የከብት ብዛት ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ የተከሰተ ችግር እንደሆነ ገልፀዋል። የመኤሶና የፈንታሌ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት ኃላፊዎች ባለፉት ሶስት ዓመታት/2000-2003/ ከፍተኛ የመኖ ችግር መኖሩን ገልፀውልናል። ይህንንም ችግር ለመቅረፍ የተጀመረ ሥራ እንዳለና እርሱም እያንዳንዱ መሬት ለግጣሽ፣ ለእርሻ፣ ለመኖሪያ እና ለደን ተብለው እየተለዩ ያሉበት ሁኔታ፤ የህዝብ ብዛት መጨመር እና አረሙንም የማስወገድ ሥራ በመንግስት፤ መንግስታዊ ባልሆኑና በኮሚሽኑ/በኦሮሚያ አርብቶ አደር ኮሚሽን/ ደረጃ በዕቅድ ያለ ስለሆነ ችግሩ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሚቀንስበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ብለዋል። በመኤሶም ወረዳ ችግሩን ለመቅረፍ ጭድ ኮንትሮባንድ በማስገባት አርብቶአደሩ ገዝቶ እዲጠቀም መደረጉን አሳውቀዋል።

**26.** በአርብቶአደሩ አካባቢ በአብዛኛው ለእንስሳት መኖነት የሚጠቀሙት የግጦሽ መሬት ነው። ይህም ሌላ የተሻሻሉ የመኖ አቅርቦት በአብዛኛው ስለማይታይ እጥረቱን እንዲባባስ እና የከብቶች ሞት እንዲጨምር አድርጐታል። የሰብል ተረፈ ምርትን በተወሰነ የመጠቀም ዘዴ ያለ መሆኑን የፈንታሌ ወረዳ አስተዳደር ቢገልፁልንም አጠቃቀሙ በተለምዶ አጭዶ የመመገብ ብቻ እንጂ የማመጣጠን ዘዴን እንደማይጠቀሙና የመኖ አቅርቦት ችግርን በሚያስወግድ መልኩ አለመሆኑ ታውቋል።

**27.** በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው የመኖ እጥረት እንዳለ ቢታወቅም በዚህ ዙሪያ የታቀዱ ዕቅዶች ግን አሉ። አንደኛ የተፈጥሮ ግጦሽን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ጠብቆ ህብረተሰቡ ሳሩን አጭዶ የመመገብ ወይም አዘዋውሮ የማስጋጥ ዘይቤን እንዲከተሉ ማድረግ /ለ2004 ዓ.ም በአፋር ክልል ሊሰራ ታቅዷል/፣ በሁለተኛ ደረጃ አርብቶአደሩ የመኖ ዘርን በመዝራትና መኖን በማልማት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ናቸው። ይህን ለማድረግም በቅድሚያ የህብረተሰቡን አመለካከት መቀየር በመሆኑ በሰፊው ባይሆንም ጅምር ስራዎች እንዳሉ ገልፀዋል።

28. አርብቶአደሩ የከብቶች መኖ ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ምግባቸውን ወደ ሚያገኙበት ራቅ ያለ አካባቢ እንዲሄዱ ያስገድዳቸዋል ይህም ለከብቶቹ መክሳት፣ የሞት መንስኤ መሆኑ፣  ለገበያ አቅርቦት ሳቢ አለመሆናቸው እና ቆዳቸውም ሳይቀር በገበያ ተፈላጊ እንዳይሆን ማድረጉና ከብቶቹም መስጠት የሚገባቸውን ውጤት ሊያስገኙ ያልቻሉበት ሁኔታ እንዳለ ታውቋል፡፡

**የመኖ ባንኮች በአርብቶአደሩ አካባቢ መቋቋማቸውን በተመለከተ:-**

29. በአርብቶአደሩ አካባቢ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት ከብቶችን ለመመገብና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የመኖ ክምችት ሊኖር ይገባል፡፡ መኖዎችንም ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመኖ ባንኮች በየወረዳው ሊቋቋሙ ይገባል፡፡

30. ነገር ግን የኦዲት ቡድኑ የመስክ ጉብኝት ባደረገባቸው በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል አርብቶአደር ወረዳዎች የመኖ ባንኮች የሌሉ መሆኑንና በሁሉም በዕቅድ ደረጃ እንኳን ለማቋቋም የታሰበ አለመሆኑን ነው፡፡

31. በአፋር ክልል በገዋኔ፤ በአሳኢታ እና በዱብቲ ወረዳዎች የመኖ ባንክ የተቋቋመ መሆኑ የተገለጸልን ሲሆን፤ በአፋምቦ ወረዳ አንድ የመኖ ባንክ እንደነበርና አሁን ግን አገልግሎት መስጠት ማቆሙን፤ በሱማሌ ክልል በጅጅጋ፤ በጉርሱም እና በአቡበሬ ወረዳዎች የመኖ ባንክ ያልተቋቋመ ሲሆን በቀብሪበያ የመኖ ባንክ የተቋቋመ ቢሆንም ሥራ አለመጀመሩ ታውቋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል  በሚኤሶ እና በፈንታሌ ወረዳዎች የመኖ ባንክ አልተቋቋመም፡፡

32. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የየክልሉ እና የየወረዳዎቹ ኃላፊዎች የመኖ ባንኮች ያልተቋቋሙበትን ምክንያት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ:- የሱማሌ ክልል የእንስሳት ሰብልና ግብርና ቢሮ ኃላፊ ተጠይቀው በአካባቢው ያለው የአመጋገብ ባህል ያላደገና በባህላዊ የአጋጋጥ ዘይቤ የሚጠቀሙ በመሆኑና ይህንንም የመኖ ባንክ ለመገንባት እስካሁን ባለው ሂደት መስራት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ መሬቶችን በመከለል ሣር እንዲበቅልበትና አጭደው መመገብ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጅምር ሥራ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡ በአሳኢታ ወረዳ ከተቋቋመው የመኖ ባንክ በተጨማሪ ግለሰቦች በድርቅ ጊዜ የሚያገለግል የራሳቸው የሆነ የመኖ ክምችት ለመያዝ ጥረት እንደሚያደርጉና በዱብቲ ወረዳ 14 ሄክታር ሣር ታጭዶ ለአርብቶአደሩ በድርቅ ጊዜ እንደተሰጠና በ2003 ግን እንዳልተሰራበት ገልፀዋል፡፡

33. በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ተወካይንም ስንጠይቅ ያገኘነው ምላሽ፤ የመኖ ባንኮች በስፋት ባይሰሩም በተወሰነ መልኩ አርብቶአደሩ ዘርን ወስዶ እየዘራ ሳሩን በማጨድ

ለከብቶች በመመገብና ዘሩንም በመሸጥ እየተጠቀመ ይገኛል። በተለይ በአፋር ጅምር ስራዎች አሉ። የአርብቶ አደሩ የአኗኗር ዘይቤ የተበታተነ መሆኑ ለስራው አስቸጋሪነቱን ያሳያል። የአርብቶ አደሩ የአኗኗር አቅጣጫ መለወጥ እንዳለበት እንደ መርህ የተያዘ ቢሆንም ይህ ደግሞ ቀላል እንዳልሆነና ወደፊት በስፋት ለመስራትና ለማጠናቀር እየተሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

**34.** የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊዎችም የመኖ ባንክ ዝግጅትን በተመለከተ በፌዴራል ግብርናና በክልሎቹ በ2003 የተጀመሩ ስራዎች ሲኖሩ በ2004 ተጠናክሮ እንዲቀጥል ክትትል ይደረጋል ብለዋል።

**35.** ይህም አርብቶአደሩ አካባቢ የመኖ ባንኮች ባለመኖራቸው የተከሰተው የመኖ እጥረት ለብዙ የዳልጋ ከብቶች መሞት ምክንያት ሆኗል።

## <u>የተሸሻለ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም ስልት/ ሥርዓት ስለመኖሩ:-</u>

**36.** የተፈጥሮ ግጦሽን መሬትን ማዳበሪያ በመጠቀም አዟዙሮ እና እንዲብቃቃ በገደብ የማስጋጥ ስርዓት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል። በተጨማሪም የተለያዩ የመኖ እፅዋት ዘሮችን በመዝራት፤ በተፈጥሮ የሚገኙት ተፈላጊ እፅዋቶች ዘር አፍርተው እንዲባዙ እድል መስጠት፤ በአላስፈላጊ አረሞች እንዳይወረሩ መቆጣጠር እና በመስኖ ሊለሙ ይገባል። በዚህ ጉዳይ ላይ ኃላፊነት ያለባቸው የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን ለይተው እንዲታወቁና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣታቸው ክትትል ሊደረግ።

**37.** በኦዲቱ ወቅት አርብቶአደሩ የሚጠቀመው የአጋጋጥ ዘይቤ የልቅ ግጦሽ መሆኑ፤ የግጦሽ መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ መምጣቱ፣ ያለው የግጦሽ መሬትና የእንስሳት ብዛት የማይጣጣምና ከልክ በላይ ከብቶች የሚሰማሩበት መሆኑ ታውቋል። ለግጦሽ ከሚውለው መሬት በኦሮሚያ አርብቶአደር አካባቢ እና በአፋር ክልል በፊት የግጦሽ ይውል ከነበረው መሬት ሃምሳ በመቶ/50%/ በአላስፈላጊ አረሞች መወረሩ ታውቋል።



ፎቶ፡-1 በኦሮሚያ ክልል ፈንታሌ ወረዳ የፓርቲኒየም(Partenium) አረም በግጦሽ መሬት ላይ በስፋት በቅሎ የሚያሳይ ምስል፡፡



ፎቶ፡-2 በኦሮሚያ ክልል ሚኤሶ ወረዳ በአሰቦት ቀበሌ በስፋት ተንሰራፍቶ ያለ የፕሮሶፒስ(Prosopis) አረምን የሚያሳይ፡፡

38. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልልና የወረዳ ኃላፊዎች ተጠይቀው በኦሮሚያ ክልል የአርብቶ አደር ኮሚሽን ኃላፊዎች ይህ የሆነበት ምክንያትን ሲገልጹ መታረስ የሌለባቸው የግጦሽ መሬቶች እየታረሱ መሆኑ፣ የእንስሳት ቁጥር እየጨመረ መምጣቱና አረሞች ከመጠን በላይ በግጦሽ መሬቶች ላይ የሚታዩ መሆኑ፣ የግጦሽ መሬት አስተዳደርም ስለሌለና ባህላዊው/የጋራ/ ዘዴ በሥራ ላይ በመዋሉ ነው ብለዋል፡፡ ይህንንም ችግር ለማቃለል በአርብቶአደር ማህበረሰብ ልማት ኘሮጀክት፣ በሌሎች መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በኮሚሽኑ አማካኝነት ሊሰሩ የታቀዱ የአረም ማጥፋትና ሌሎች ሥራዎች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

39. በኦሮሚያ ክልል የፈንታሌና የመኤሶ ወረዳዎች አስተዳደር እና የወረዳዎቹ አርብቶ አደር ጽ/ቤቶች፣ በአፋር ክልል በአብዛኛው ወረዳዎች ኘሮሶፒስ (Prosopis) በመባል የሚታወቀው የአረም አይነት በከፍተኛ ደረጃ እንዳለና ከወረዳዎቹ ከቁጥጥር ውጪ እንደሆነ የአፋር ክልል ግብርና ቢሮ፣ በክልሉ በናሙና የታዩት ወረዳዎች የአስተዳደር እና የአርብቶአደር ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

40. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ የግጦሽ መሬት አስተዳደር ስርዓት ሙሉ ለሙሉ የለም ማለት ባይቻልም የታዩት ችግሮች ለረዥም ጊዜ የቆዩና ከህብረተሰቡ ባህልና አኗኗር ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህንንም ስር የሰደደ ችግር ለመፍታትም በየክልሉ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫና የሰርቶ ማሳያ ስራዎች በመካሄድ ላይ የሚገኙ ሲሆን የመጤ አረም ችግር በጣም ሰፊ መሆኑን ጠቅሰው በቀጣይ ችግሩን በጥናት ላይ ተመስርቶ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴርና በክልሎች በዕቅድ ተይዞ በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

41. በግጦሽ መሬቶች ላይ አላስፈላጊ አረሞች በስፋት መታየታቸው እና ችግሩንም ለማስወገድ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦች በመዘግየታቸው በአርብቶ አደሩ አካባቢ ላሉ የዳልጋ ከብቶች የሚሆነውን የግጦሽ መሬት እንዲያንስ እና የመኖ እጥረት እንዲከሰት ከማድረጉም በተጨማሪ ለዳልጋ ከብቶች መክሳትና መሞት ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>በአርብቶአደሩ አካባቢ ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን ንፁህ የመጠጥ ውሃ ስለመኖሩ፡-</u>

42. በአርብቶአደሩ አካባቢ ለሚገኙ የዳልጋ ከብቶች የዝናብ ውሃን በማቆር፣ መስኖን በመጥለፍ፣ አነስተኛ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን በማስቆፈር ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲሻሻል የፌዴራልና የክልል ሴክተር መ/ቤቶች በመቀናጀት የውሃ አቅርቦቱ እንዲሟላ ማድረግ አለባቸው፡፡ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርም የማስተባበር እና የመከታተል ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

43. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ ወረዳዎች ባደረገው የመስክ ጉብኝት፡- በኦሮሚያ ክልል በፈንታሌ ወረዳ ኢላላ ቀረሪ ቀበሌ ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንደሌለና ያለውም የኩሬ ውሃ የደረቀ መሆኑን፣ በሶማሌ ክልል ጅጅጋ ወረዳ በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት የተገነባው የኩሬ ውሃ/ማጠራቀሚያ ገንዳ/ የደረቀ በመሆኑ ከብቶች ብዙ ኪሎ ሜትር ውሃ ለመጠጣት ሲጓዙ እንደሚውሉ ቡድኑ ያነጋገራቸው አርብቶ አደሮች የገለጹ መሆኑ እና ሁኔታውን ቡድኑ በአካል ተገኝቶ ተመልክቷል፡፡

44. አርብቶ አደሮቹም የከብቶቻቸውንም ሆነ የራሳቸውን ዕድሜ ለማራዘም ከሌላ ቦታ በከፍተኛ ዋጋ በቦቴ በመግዛትና በማስመጣት ወደ ጉድጓዱ በመገልበጥ ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት እንደሚያደርጉ ታውቋል፡፡



ፎቶ፡3 በሱማሌ ክልል በጅጅጋ ወረዳ በአመሌ ቀበሌ ህብረተሰቡ ውሃ ከሌላ ቦታ በቦቴ አስመጥተው ወደ ጉድጓድ ሲያስገለብጡ የሚያሳይ፡

45. በቀብሪበያ ወረዳ አርትሼክ ቀበሌ ሾካ በሚባል ድርጅት የተሰራ የእንስሳት የገበያ ማዕከል እንዲያገለግል የተገዛ 1000 ሊትር የሚችል የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር/ሮቶ/ ያለአገልግሎት ስራ ሳይጀምር እንደቀረ በቀበሌው የእንስሳት ጤና ኬላ ረዳት ሃኪም ተገልፆልናል የኦዲት ቡድኑም ተመልክቷል።



ፎቶ፡-4 በሱማሌ ክልል ቀብሪበያ ወረዳ አርቲሼክ ቀበሌ ከክሊኒኩ አሸንዳ ጋር ሳይገናኝና ለአገልግሎት ዝግጁ ሳይሆን የተቀመጠ  የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር።

46. ስለጉዳዩ ተጠይቀው የሱማሌ ክልል የእንስሳት ሰብል እና ግብርና ቢሮ ባለሙያዎች በጋራ በሰጡት ምላሽ ችግሩ ያለና እውነት መሆኑን ጠቁመው የችግሩ መንስኤ የተቆፈሩት የኩሬ ጉድጓዶች ውሃ የመያዝ አቅማቸው ውሱን መሆን፣ የሚሰሩትም ኩሬዎች በጊዜያዊነት እንጂ ቀጣይነትን መሰረት ያላደረጉ መሆኑ፣ የሚገነቡት ቢርካዎች ለሰውና ለእንስሳት አንድ በመሆኑ እና ዝናብ መዝነብ በሚገባው ወቅት ባለመዝነቡ ምክንያት ኩሬዎች ውሃ በውስጣቸው እንዳይገኝ አድርጎታል ብለዋል። ነገር ግን ይህን ችግር ለማቃለል ክልሉ የጥልቅ ጉድጓድ ውሃ የሚቆፍሩ ማሽኖች ግዢ ፈፅሞ ወደ ተግባር ለመግባት በሂደት ላይ መሆኑን ገልፀዋል። በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የተመጣጣኝ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክቶሬትም ችግሩ መኖሩንና ችግሩንም ለመቅረፍ መንግስት ተፋሰሶችን መሰረት ያደረገ የማስፈር ስራ ለመስራት በዕቅድ የተያዘ መሆኑንና ጅምር ስራዎች ያሉ መሆኑን ገልፀዋል።

47. የውሃ አቅርቦቱ ባለመሟላቱ ከብቶች ውሃ ለማግኘት ሲጓዙ እንደሚውሉና ከጠጡም በኋላ ከሁለት ቀናት በፊት እንደማይመለሱ እና ለክሳትና ለሞት እንዲዳረጉ አድርጓቸዋል።

## የተሻሻሉ የዳልጋ ከብት ዝርያዎችን ማራባትና ማስራጨትን በተመለከተ:-

**48.** በሀገር ውስጥ በሥጋና በወተት ምርታቸው የተሻለ ሕብለ በራሄ(Genetic potential) ያላቸው የዳልጋ ከብቶችን ዝርያቸው ሊራቡና ውጤታማ የሆነ የአረባብ ዘዴን አርብቶአደሩ እንዲከተል ሊደረግ ይገባል፡፡ ለአርብቶአደሩ በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የዳልጋ ከብት በብዛትና በጥራት በማራባት የአርብቶ አደሩ ኑሮ ሊሻሻል ይገባል፡፡ ይህንንም ለማገዝ ከሀገር ውስጥ የምርምር ተቋማትና ከውጭ ሀገር በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ላይ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ ለአርብቶአደሩ ህብረተሰብ እንዲሰራጩ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡

**49.** ይሁን እንጂ በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው በኦሮሚያ፤ በሱማሌ እና በአፋር ክልል በተመረጡ ወረዳዎች የተሻለ ዝርያ ያላቸውን የዳልጋ ከብቶችን የማራባትና የመጠቀሙ ሁኔታ ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የከብት ቁጥርን ሳይጨምር የተሻሻለ ዝርያ ያላቸውን የዳልጋ ከብቶች በመጠቀም እና ውጤታማ የሆነ የአረባብ ዘዴን በመከተል የተሸለ ጥቅም ማግኘት ይቻላል የሚለው ሀሳብ በአርብቶአደሩ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ የተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ አነስተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአፋር ክልል በአፋምቦ ወረዳ ለአንድ ሞዴል አርብቶአደር የቦረና ዝርያ ያላት አንዲት ላም ተሰጥቶአቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢደረግም ክትትል ያልተደረገላቸው መሆኑን ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

**50.** ስለጉዳዩ የየወረዳው የእንስሳት ሰብል እና ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ በሱማሌ ክልል የጅጅጋ፣ የአቡበሬ፣ የጉርሱም፣ የቀብሪበያ ወረዳዎች፣ በኦሮሚያ ክልል የፈንታሌ እና የሚኤሶ ወረዳዎች ላይ የማራባትና የማስራጨት ሥራው ሊሰራ ያልቻለበት ምክንያት:- ዘርፉ ውድ በመሆኑ አርቢው ህብረተሰብ በፍጥነት አምኖበት ወደ ሥራው ሊገባ ባለመፈለጉ፣ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ከብቶች እርባታ ውጤቱ የሚታየው በረዥም ጊዜ በመሆኑ ለዚህም የረጅም ጊዜ ብድር አገልግሎት ያልተመቻቸ በመሆኑ፣ በአካባቢው የመኖ እጥረት በመኖሩና ድርቅን የመቋቋም አቅማቸው አነስተኛ በመሆኑ ለሞት ይዳረጋሉ የሚል ሥጋት በመኖሩ፣ በአርብቶአደሩ ዘንድ የማዳቀል አገልግሎት በፈጣሪ ሥራ ጣልቃ እንደተገባ አድርጎ የመመልከት እና ወደ ተግባሩም ደፍሮ ያለመግባት እንደ ትልቅ ምክንያት መሆናቸውን አቅርበዋል፡፡

**51.** በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የተመጣጣኝ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርም ይህንኑ ሀሳብ ከመጋራት በተጨማሪ አርብቶ አደሩ በአዕምሮው ያለው "ብዛት" የሚለው ሀሳብ በመሆኑ ነው፡፡

**52.** አርብቶ አደሩ በከብት ርባታው ላይ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ማርባት አለመቻሉ፤ ከምርቱ ተጠቃሚ አለመሆኑና ኑሮው እንዳይሻሻል ማድረጉ ናቸው፡፡

**<u>በአርብቶ አደር ወረዳዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚደረገው የጤና አገልግሎትን በተመለከተ፡-</u>**

**53.** በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያሉ የዳልጋ ከብቶች የጤና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ ይህንን ለማድረግ የእንስሳት ኪሊኒኮች ሊገነቡና በአስፈላጊው የሰው ኃይል፣ በመድኃኒት እና በመገልገያ መሳሪያዎች ሊሟሉላቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአካባቢው ለሚከሰቱ የወረረሽኝ በሽታዎች መከላከያ የክትባት አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደርግ አለበት፡፡ ይህንን አገልግሎት ለአርብቶአደሩ ለማዳረስ የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት ሊሰሩ ይገባል፡፡

**54.** ሆኖም በናሙና ከተመረጡት በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ ወረዳ 9 ክሊኒኮች ያሉ ቢሆንም የሚያስፈልገው ግን 46 መሆኑና አንድ የእንስሳት ክሊኒክ ተገንብቶ ያለ አገልግሎት ከአንድ ዓመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፣ በሱማሌ ክልል ቀብሪበያ ወረዳ ክሊኒክ የሌለ ሲሆን 24 ጤና ኬላ መኖሩና አንድ የኦዲት ቡድኑ የተመለከተው የጤና ኬላ አሰራሩ ደረጃውን ያልጠበቀና ፈራርሶ በዝናብ ወቅት ውሃ የሚያስገባ መሆኑ እና በአፋር ክልል/ ገዋኔ ወረዳ 1 ክሊኒክ ያለ ሲሆን የጤና ኬላ የሌለ መሆኑ፣ በሚሌ ወረዳ ክሊኒክ የሌለ ሲሆን አምስት የጤና ኬላ ያሉ ቢሆንም አገልግሎት የሚሰጠው አንዱ ብቻ መሆኑ፣ በአፋምቦ ወረዳ 1 ክሊኒክና 5 በግንባታ ላይ ያሉ ጤና ኬላዎች የሚገኙ መሆኑ እና በአሳኢታ ወረዳ 1 ክሊኒክና 2 ጤና ኬላዎች ያሉ ቢሆንም የሚያስፈልገው ግን 4 ክሊኒክና 7 ጤና ኬላዎች መሆናቸው እና ያሉት ክሊኒኮች በሰው ኃይልም ሆነ በመድኃኒት አቅርቦት ያልተሟሉ መሆኑ ታውቋል፡፡



ፎቶ፡- 5 በሱማሌ ክልል ቀብሪበያ ወረዳ የእንስሳት ክሊኒክ መድሃኒት ቤት ፈራርሶና በክረምት ወራት ዝናብ ሊያስገባ የሚችል መሆኑን የሚያሳይ፡፡

**55.** የመድሃኒት አቅርቦትን በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ ወረዳ፤ ሱማሌ ክልል ጅጅጋ፣ ጉርሱም፣ አቡበሬና ቀብሪበያ ወረዳዎችና በአፋር ክልል በሚሌና አሳኢታ ወረዳ የመድሃኒት አቅርቦት ውስንነት መኖሩ፣ በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ ወረዳ፣ በአፋር ክልል አፋምቦና በአሳኢታ ወረዳዎች የክትባት አቅርቦት ውስንነት መኖሩ፣ ሱማሌ ክልል ጉርሱም፣ አቡበሬና ቀብሪበያ ወረዳዎች አና በአፋር ክልል አሳኢታ ወረዳ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች አለመሟላታቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በፈንታሌ ወረዳ እንዳሉ ተለይተው ለታወቁ የበሽታ አይነቶች አላስፈላጊ መድሃኒቶች በክልሉ ተገዝቶ የሚመጣ ከመሆኑም በላይ ለመበላሸትና የአገልግሎት ጊዜያቸው እያለፈባቸው የመድሃኒት መደብሮችን አጣብበው መገኘታቸውን ለማየት ተችሏል፡፡



ፎቶ፡-6 በኦሮሚያ ክልል በፈንታሌ ወረዳ በእንስሳት ክሊኒክ ውስጥ ለቦቫይን ፓስትሮሎሲስ (bovine pastreulosis) በሽታ ህክምና የሚውል የክትባት መድሃኒት የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት፡፡

**56.** በሚኤሶ ወረዳ የተጠቀሱትን ችግሮች አስመልክቶ ለኦሮሚያ አርብቶአደር ኮሚሽን የኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት አስተባባሪ ተጠይቀው የገለፁት፤ ክሊኒኮች ተገንብተው ካለቁ በኋላ ወደ ስራ የማይገቡበት ሁኔታ ስለመኖሩ ጠቅሰው ይህ የሆነበትን ምክንያት በዝናብ እና ኮንትራክተሮች ባለማስረከባቸው ነው፡፡ የእንስሳት ባለሙያዎችን በተመለከተ እጥረት መኖሩን እና ለዚህም እንደ ምክንያትነት የጠቀሱት አካባቢው ወጣ ያለ በመሆኑ ባለሙያዎች ከሥራ መልቀቃቸውና ወደ ሌላ የተሻለ ቦታ የሚዘዋወሩ በመሆኑ ሲሆን የከብቶች ብዛትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ በወረዳው ያሉት ክሊኒኮች ላሉት የዳልጋ ከብቶች በቂ እንዳይሆኑ ምክንያት ሆኗል፡፡

**57.** በሱማሌ ክልል በተመረጡት ወረዳዎች በክትባት፣ በመድሃኒትና በክሊኒኮች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች አስመልክቶ የሱማሌ ክልል ክሊኒካል ፊልድ አገልግሎት ኦፊሰር ችግሮቹ ያሉ ቢሆኑም ሊስተካከሉ የሚችሉት በወረዳዎቹ ነው፡፡ የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊነት ለወረዳው የሚያስፈልገውን በጀትና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

**58.** በአፋር ክልል በተመረጡት ወረዳዎች በክትባት፣ በመድሃኒትና በክሊኒኮች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች አስመልክቶ የክልሉ አርብቶ አደር ግብርና ልማት ዘርፍ ባለሙያ የክሊኒኮች ግንባታን በተመለከተ ክሊኒኮች ተገንብተው ስራ ያልጀመሩበት ሁኔታ

መኖሩን ጠቅሰው ምክንያቱ የአርብቶ አደሩን እንቅስቃሴ መሰረት አድርገው ስላልተገነቡ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

**59.** በናሙና በተመረጡት በሱማሌ፣ በኦሮሚያና በአፋር ክልል ወረዳዎች የተገኙ መረጃዎች የሚጠቁሙት የተለያዩ የበሽታ አይነቶች በስፋት የሚገኙ መሆኑን ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የአፍተግር/FMD/፣ አባሰንጋ፣ ጎሮርሳ፣ የሳምባ ምች፣ አባጎርባ እና ቦቫይን ፓስትሪሎሲስ/Bovaine pastrioulosis/ የሚባሉት እንደሚገኙ ካነጋገርናቸው የየወረዳ አርብቶአደር ፅ/ቤት ባለሙያዎች ተገልፆአል፡፡

**60.** በክትባት፣ በመድሃኒትና በክሊኒኮች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች አስመልክቶ በግብርና ሚኒስቴር ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የእንስሳት ህክምና ኤክስፐርት እና በፌዴራል ጉዳዮች የተመጣጣኝ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እንደገለፁት በነዚህ አካባቢዎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱ እና በመድሃኒት አቅርቦት ዙሪያም ስለሚሰሩ እጥረት አለ ለማለት ባያስችልም በክልሉ የሚገዙ መድሃኒቶችም በስርጭት ወቅት በሚከሰቱ ችግሮች ተደራሽነቱን ሊቀንሱት ይችላሉ፡፡

**61.** በሱማሌ ክልል በቀብሪበያ ወረዳም የክትባት አገልግሎት በዓመት 2 ጊዜ ለመስጠት ዕቅድ ቢያዝም ያልተሰጠ መሆኑ፣ በአርብቶአደሩ ዘንድ የግንዛቤ እጥረት በመኖሩና በሰው ኃይል እጥረት ችግር ምክንያት የክትባት አገልግሎት በስፋት አለመሰጠቱን የወረዳው የእንስሳት ጤናና ኘሮዳክሽን ኃላፊ ገልፀዋል፡፡ የክትባት እና የመድሃኒት አቅርቦትና ስርጭት ውሱንነት፣ የባለሙያዎች እጥረት፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች አለመኖር እና የክሊኒኮች በተሟላ ሁኔታ አገልግሎት አለመስጠት በአካባቢው በዛ ያሉ በሽታዎች ተንሰራፍተው እንዲገኙ ከማድረጉም በላይ የዳልጋ ከብት ጤና ሽፋን አነስተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

**<u>ለአርብቶአደሩ ከዳልጋ ከብት ምርትና ምርታማነት ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በተመለከተ፡-</u>**

**62.** በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ላይ ለተሰማሩ አርብቶአደሮች እና ባለሞያዎች የዳልጋ ከብት ምርታማነትን በማሳደግ ዙሪያ ሥልጠና ሊያገኙ ይገባል፡፡ ሥልጠናውም ስለ እንስሳት ጤና አጠባበቅ፣ ስለተሻሻሉ መኖዎች አጠቃቀም፣ የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች አረባብ ዘዴን ጤና አጠባበቅ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያ እና ደንብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲፀድቅና የፀደቀውንም ለእንስሳት አርቢው ህዝብ ግንዛቤ ማስጨበጥና ሥራ ላይ እንዲውሉ ሙያዊ ድጋፍ ሊሰጡ ይገባል፡፡

63. ሆኖም የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡትና ጉብኝት ባደረግንባቸው በሱማሌ ክልል ጅጅጋ፣ አቡበሬ፣ ቀብሪበያና ጉርሱም ወረዳዎች፤ በአፋር ክልል ገዋኔ፣ አሳኢይታ ዱብቲና ሚሌ ወረዳዎች እና በኦሮሚያ ክልል ሚኤሶ ወረዳ በመኖ ልማትና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በመረጃ የተደገፈ አለመሆኑና በአፋር ክልል በአፋምቦ ወረዳና በኦሮሚያ ክልል በፈንታሌ ወረዳ ስልጠናዎች ያልተሰጡ መሆኑ ተገልጾልናል፡፡

64. ይህን አስመልክቶ የየክልሉ የአርብቶ አደር ግብርና ልማት ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ በእንስሳት አረባብ ዘዴ፣ በመኖ አያያዝና አመጋገብ በጤና አጠባበቅ ዙሪያ ለአርብቶ አደሩ እና ለባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል ነገር ግን በመረጃ የተጠናቀረ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

65. ለባለሞያዎችም ሆነ ለአርብቶአደሩ ስልጠናዎች በአግባቡና ወጥነት ባለው መንገድ አለመሰጠቱ ባለሞያዎች ወቅታዊ በሆነ ዕውቀት እንዳይሰሩ ማድረጉ ሲሆን አርብቶአደሮችም ዘመናዊ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም እንዳይከተሉ፣ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮችን በስፋት እንዳይጠቀሙ ማድረጉና በከብት ብዛት ላይ እንጂ ጥራት መሰረት ያደረገ የአረባብ ዘዴ እንዳይጠቀሙ አድርጓል፡፡

## <u>በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎች የሚጠናከሩበት ሥርዓት ስለመኖሩ:-</u>

66. በአርብቶአደሩ አካባቢ በየደረጃው ለሚደረግ የክትትልና ግምገማ ሥራ እንዲሁም ለሚቀየሱ ፕሮጀክቶች ጥናት በመነሻነት የሚያገለግል የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንዲኖር ማድረግ ይገባዋል፡፡ መረጃው የእንስሳትን ብዛት፣ የመኖ ፍላጐትና አቅርቦት መጠን፣ የበሽታ አይነቶችንና የሞት መጠን፣ የሞያተኞች አይነትና ብዛት ወዘተ የሚያካትትና በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ ባየናቸው የሱማሌና የአፋር ክልል እና የኦሮሚያ አርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ወጥነት የሌለውና የመረጃ ስርዓት የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ በሱማሌ በክልል ደረጃ ያሉትን የዳልጋ ከብቶች ብዛት የሚያሳይ መረጃ፣ ምን ያህል መኖ በአካባቢው ላለው ከብት እንደሚያስፈልግና እጥረቱ የሚታወቅበት ሥርዓት፣ ለአርብቶ አደሩ በየጊዜው የተሰራጨ የመኖ ዘሮች (የመኖ ዕፅዋት ቁርጥራጮችን ጨምሮ) መጠን በኪሎም ሆነ በቁጥር አይታወቅም፡፡ በተጨማሪም በአካባቢው ያለውን የዳልጋ ከብት የሞት መጠን እና ሞቱ የተከሰተበትን ምክንያት እየተመዘገበና እየተተነተነ የሚጠናቀርበትና የሚያዝበት ሥርዓት የለም፡፡

68. ይህን አስመልክቶ በግብርና ሚኒስቴር ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ ያሉትም ዳይሬክቶሬቱ እራሱን ችሎ ከተቋቋመ በኋላ በሱማሌና በአፋር ክልል ያሉ የዳልጋ ከብቶች መረጃ ሲኖር የቤንሻንጉል ጉምዝና የጋምቤላ የሌለና አሁን ግን መረጃ በማሰባሰብ ላይ እንደሚገኙና የሱማሌና የአፋርን መረጃ ያገኙትም በክልሉ ካሉ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ሠራተኞች መሆኑን ገልፀው ይህም ሆኖ ህዝቡ በራሱ ከብቱን ማስቆጠር ፍቃደኛ ባለመሆኑ የተጠናቀረ የመረጃ ስርዓት የሌለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

69. በየወረዳዎች የተጠናቀረ የመረጃ ሥርዓት ባለመኖሩ የተለያዩ አካላት ዘርፉን በተመለከተ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ካነጋገርናቸው የወረዳ ኃላፊዎች ተገልያልናል፡፡ በተለይም በመኖ አቀርቦት፣ በእንስሳት የሞት መጠን፣ በእንስሳት ክሊኒኮችና የጤና ኬላዎች አለመታወቅ ምን ላይ መደረስ እንደሚገባ ለማመልከት አስቸጋሪ ያደረገው መሆኑ ታውቋል፡፡

__በአርብቶአደሩ አካባቢ የዳልጋ ከብት ልማትን የሚደረገውን እገዛ በተመለከተ:-__

70. ለአርብቶአደሩ የሚያደርገው የልዩ ድጋፍ ሥራ ከእንስሳት ሃብት ልማት ጋር በተያያዘ የአርብቶአደሩን የፍላጐት እና የአቅርቦት የአቅም ክፍተትን ጨምሮ በቅድሚያ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡ በጥናት የተለዩትን ክፍተቶች መሰረት በማድረግ አስፈላጊው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ለዚህም የሚያግዙ የተለያዩ ፓኬጆች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡

71. ይሁን እንጂ ለአርብቶአደሩ የሚደረገው የልዩ ድጋፍና የልማት ትብብሩ የእስካሁን ሂደት የአርብቶአደሩን መሰረታዊ ፍላጐትና የአቅም ክፍተት መሰረት ያላደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኦሮሚያ፣ ሱማሌና አፋር ክልል በተመረጡ አርብቶ አደር ወረዳዎች ከኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እና በመስክ ጉብኝት የአቅም ክፍተት መኖሩን ገልፀዋል፡፡ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አማካኝነት የተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶች የተጠና ቢሆንም የአርብቶአደሩ ፍላጐት በተለይም በውሃ አቅርቦት ላይ ክፍተቱ ያለ መሆኑን እና አለመቀረፉን በጅጅጋ ዙሪያ ወረዳ የኦዲት ቡድኑ ካነጋገራቸው አርብቶ አደሮች ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. በአርብቶ አደሩ ክልሎችና አካባቢዎች የመኖ እጥረት፣ የተለያዩ በሽታዎች በስፋት መኖራቸው እና አላስፈላጊ አረሞች /በአፋር ክልልና በኦሮሚያ ክልል ፈንታሌና ሚኤሶ ወረዳዎች/ በስፋት መኖራቸው ትልቅ ችግር እንደሆነ ቢታወቅም ችግሮቹ እስካሁን ያሉ መሆናቸውን የየወረዳዎቹ የአርብቶ አደር ፅ/ቤት ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

**73.** ይህን አስመልክቶ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ለተመጣጣኝ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርም የሰጡት ምላሽ በክልል ደረጃ ችግሩ ያለ ቢሆንም፤ የችግሩ ምክንያት በዘንድሮው ዓመት በክልሉ ዝናብ መዝነብ በሚኖርበት ወቅት ባለመዝነቡ የውሃ እጥረት እንዲከሰት ከማድረጉም በላይ በሱማሌና በቦረና ዞን ለከብቶች ሞት ምክንያት ሆኖአል፡፡ የውሃ ኩሬዎችን ስፋት በተመለከተ ኘሮጀክቱ ሲሰራ ከህብረተሰቡ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ የተመረኮዘና የስፋቱ መጠንም በሚገኘው የገንዘብ መጠን ላይ የሚወሰን በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ችግር በዘለቄታው ለመቋቋም የታቀደው፤ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቱን ማጠናከር እና ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የሰፈራ ኘሮግራም ማከናወን ነው፡፡

**74.** በናሙና በተመረጡት ወረዳዎች ያሉት ዋና ዋና ክፍተቶች ባለመሞላታቸው አርብቶ አደሩ ያለውን የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዘለቄታ ባለው መንገድ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይራመድ አድርጎታል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ (Conclusions)

**75.** የአርብቶ አደሩን የዳልጋ ከብት ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የመኖ፣ ግጦሽ መሬትና ውሃ አቅርቦት፣ የዝርያ ማሻሻል ተግባራት በብቃት የሚከናወኑ እና ስኬታማ መሆናቸውን በተመለከተ:-

- አርብቶ አደሩ የተሻሻሉ የመኖ ዓይነቶችን የማይጠቀም መሆኑ፣
- የሰብልና የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችን የመጠቀም ሁኔታ አነስተኛ መሆኑ፣
- በፊት ያለው የግጦሽ መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ መምጣቱ፣
- የመኖ አቅርቦቱ ካለው የከብት ብዛት ጋር የሚጣጣም አለመሆኑ፣
- ለተወሰነ ጊዜ የተወሰኑ ከብቶችን መመገብ የሚችል የመኖ ክምችት የሌለ መሆኑ፣
- የመኖ ባንኮች አለመኖራቸው፣
- አላስፈላጊ አረሞች በግጦሽ መሬቶች ላይ በስፋት ያሉ መሆኑ፣
- የግጦሽ መሬትን የማልማት አረምን በተለይም የፓርቲኒየም እና ፕሮሶፒስ የሚባሉትን የማጥፋት ስራ ያልተሰራ መሆኑና እንዲለማ በዕቅድ ደረጃ ያልተያዘ መሆኑ፣
- በአርብቶአደሩ አካባቢ የግጦሽ መሬት አስተዳደር/ሥርዓት አለመኖሩ፣
- በአርብቶአደሩ አካባቢ ያለው የውሃ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ መሆኑ፣
- ከብቶች ውሃ ፍለጋ ብዙ ርቀት የሚጓዙ መሆኑና ይህም በሁለትና በሶስት ቀናት ልዩነት እንዲጠጡ ማድረጉ፣
- የተቆፈሩ የውሃ ኩሬዎች ውሃ በውስጣቸው የሌለ መሆኑ ፣
- የተቆፈሩት የኩሬ ውሃ ጉድጓዶች ውሃ የመያዝ አቅማቸው አነስተኛ መሆኑ፣
- አርብቶ አደሩ አካባቢዎች የወንዞች መዳረሻ ቢሆኑም መስኖን በመጠቀም የውሃ አቅርቦቱን የማሻሻል ሥራ ያልተሰራ መሆኑ፣
- አርብቶአደሩ የተሻሉ ዝርያ ያላቸውን ከብቶች እንዲያረቡ እና ውጤታማ እንዲሆኑ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲጠቀሙ የተሰራው ሥራ አነስተኛ መሆኑን፣

- አርብቶ አደሩ ብዛትን እንጂ ጥራትን መሰረት ያደረገ የአረባብ ዘዴ የማይጠቀም መሆኑ፣
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ የከብት ማዳቀል አገልግሎትን በእግዚአብሔር ሥራ ጣልቃ እንደተገባ አድርጎ የሚመለከት መሆኑ፣

**76.** በአርብቶ አደሩ አካባቢ የዳልጋ ከብቶች የግጦሽ አካባቢና መኖሪያ ስፍራ ጤናማ የማድረግ ስራ የሚከናወን፣ የሕክምና አገልግሎት እና የመድሐኒት አቅርቦት የተሟላ መሆኑን በተመለከተ:-

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያሉት ክሊኒኮች ላሉት የዳልጋ ከብቶች በቂ አለመሆናቸው፣
- ያሉት ክሊኒኮች በሰው ኃይልና በህክምና መገልገያ መሣሪያ ያልተሟሉ መሆናቸው፣
- ተገንብተው ሥራ ያልጀመሩና የፈራረሱ ክሊኒኮች መኖራቸው፣
- የመድሃኒት አቅርቦትና ሥርጭት ውሱን መሆኑ
- የክትባት አገልግሎት በወቅቱና ቀጣይነት ባለው መንገድ የማይሰጥ መሆኑ፣
- የተለያዩ የእንስሳት በሽታዎች ያሉ መሆኑ፣
- ክሊኒኮች ሲገነቡ ከአርብቶ አደሩ አካባቢ ራቅ በማለታቸው የህክምና አገልግሎቱን እንዳያገኙ ማድረጉ፣
- በወረዳዎች የተለያዩ የእንስሳት መድሃኒቶች የአገልግሎት ዘመናቸው አልፎ የመድሃኒት ማከማቻዎችን አጣበው መታየታቸው፣

**77.** የዳልጋ ከብቶች ምርታማነትና ብዛትን ለመከታተል የሚያስችል የክትትልና የመረጃ አያያዝ ሥርዐት መዘርጋቱን፣ ለአርብቶአደሩ ሕብረተሰብ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና የሚሰጥበት ስርዓት መኖሩንና ተፈፃሚ መደረጉን እና ለአርብቶ አደሩ የሚደረገው ልዩ ድጋፍ የአርብቶ አደሩን መሰረታዊ ፍላጎት ያሟላ መሆኑን በተመለከተ:-

- የዳልጋ ከብቶች ሀብት ልማትን ለማሻሻልና ከዘርፉ የተሻለ ውጤት ለማግኘት እንዲያስችል የሚረዱ ማኑዋሎች እና ከዘርፉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች ለአርቢው ህብረተሰብ እና ለዘርፉ ባለሙያዎች የማይሰጡ መሆኑ፣
- የዳልጋ ከብቶች ብዛትን፣ የመኖ አቅርቦት በቶን /ኪ.ግ/፣ የተሰጡት የስልጠና አይነትና የሰልጣኞች ዝርዝር፣ የውሃ ኩሬዎች ብዛት፣ የባለሙያዎች ስም ዝርዝር፣ የዳልጋ ከብት ሞት መጠንና በምን እንደሞቱ የሚያሳይ መረጃን በተመለከተ የሚጠናቀርበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የመኖ እጥርት፣ ውሃ አቅርቦት እጥረት እና የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ችግር መኖሩ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚደረገው እገዛ የአርብቶ አደሩን መሰረታዊ ፍላጎት ያሟላ ነው ለማለት የማያስችል መሆኑ፣

ሚኒስቴሩንም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ለዳልጋ ከብት ሀብት ልማቱ የሚያደርጉትን ጥረት የሚገታ እና ከልማቱም ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ውጤት እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡

**78.** በአጠቃላይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆኑ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የዳልጋ ከብት ሀብት ልማትን ለማሻሻል እንቅስቃሴ መጀመራቸው ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ለአርብቶ አደሩ የሚደረገውን ልዩ ድጋፍና ሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ለአርብቶ አደሩ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚያከናውኑት የመኖ እና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴዎች፣ ምርታማነት እና በመጠን የማሳደግ እንዲሁም የግንዛቤ ማዳበርና የመረጃ አያያዝ ተግባራትን የማስተባበርና የማቀናጀት ሥራው ብቃት ባለው መንገድ የማይከናወን ከሆነ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙ የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች በአጠቃላይ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማትን ሊያሻሽሉ ይችላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች/Recommendation/

**79.** የአርብቶ አደሩን የዳልጋ ከብት ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የመኖ፣ ግጦሽ መሬት፣ ውሃ አቅርቦት፣ የዝርያ ማሻሻል ተግባራት በብቃት የሚከናወኑ እና ስኬታማ መሆናቸውን በተመለከተ፡-

- በክልሎቹ ወይም አርብቶ አደር አካባቢዎች ምን ያህል የዳልጋ ከብት እንዳለ ማወቅ፣ ያለው የመኖ አቅርቦት ለምን ያህሉ ይበቃል የሚሉትና ምን ያህል መኖ አሁን ላሉት የእንስሳት ብዛት ያስፈልጋል? የሚሉት ጉዳዮች በቅድሚያ መታወቅ አለበት፡፡
- የተሻሻሉ የመኖ ዘሮችን አርብቶ አደሩ የሚያገኝበት ሁኔታ ቢመቻችና ዘርተው እንዲጠቀሙ ቢደረግ፡፡
- የኢንዱስትሪና የሰብል ተረፈ ምርቶችን የሚጠቀሙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡
- አርብቶ አደሩ አካባቢ ባሉ የግጦሽ መሬቶች ላይ በቅለው የሚገኙ አላስፈላጊ አረሞችን ለማስወገድ የተለያዩ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቅንጅት የሚሰሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡
- አርብቶ አደሩ በግጦሽ መሬት አስተዳደር ላይ ያለውን ባህላዊ መንገድ/የወል ሥርዓት/ በማይነካ መልኩ የልቅ ግጦሽን በመተው አዟዙሮ የማስጋጥ እና አጭዶ የመመገብ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት መስራት አለባቸው፡፡
- በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የተወሰኑ ከብቶችን ለተወሰነ ጊዜ መመገብ የሚችል አስተማማኝ የመኖ ክምችት እንዲኖርና ለዚህም የሚያገለግሉ የመኖ ባንኮች መገንባት አለባቸው፡፡
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ላሉ የዳልጋ ከብቶች የሚሆን የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ወንዞችን በመስኖ በመጥለፍ፣ ብዙ ውሃ የመያዝ አቅም ያላቸውን የውሃ ኩሬዎችን በመገንባት እና ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን በማስቆፈር ለችግሮቹ መፍትሄ እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡

- የተሻለ ዝርያ እንዳላቸው የታወቁ የዳልጋ ከብቶች በማዳቀልም ሆነ ጊደርና ኮርማዎችን በመጠቀም አርብቶ አደሩ እንዲያረባ መጠቀም እንዲችል ስለ ቴክኖሎጂው አስፈላጊነት የሚያውቅበት መንገድ መመቻቸት አለበት፡፡

**80.** በአርብቶ አደሩ አካባቢ የዳልጋ ከብቶች የግጦሽ አካባቢ እና መኖሪያ ስፍራ ጤናማ የማድረግ ስራ የሚከናወን፣ የሕክምና አገልግሎት እና የመድሐኒት አቅርቦት የተሟላ መሆኑን በተመለከተ፡-

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ የአርብቶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ መሰረት ያደረጉ የእንስሳት ክሊኒኮች መገንባት፣ የተገነቡትም ክሊኒኮች በአስፈላጊው የሰው ሀይል/ባለሙያ፣ መድሃኒት፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያ እና በሌሎች ከህክምናው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቁሳቁሶች እንዲሟሉ የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት ቢሰሩ የጤና ሽፋኑ እንዲያድግ ያደርገዋል፡፡

- በአርብቶ አደሩ አካባቢ ባሉት አንዳንድ ክሊኒኮች ውስጥ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ጉዳት ሳያደርሱ የሚወገዱበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

**81.** የዳልጋ ከብቶች ምርታማነትና ብዛትን ለመከታተል የሚያስችል የክትትልና የመረጃ አያያዝ ሥርዐት መዘርጋቱን፣ ለአርብቶአደሩ ሕብረተሰብ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና የሚሰጥበት ስርዓት መኖሩንና ተፈፃሚ መደረጉን እና ለአርብቶ አደሩ የሚደረገው ልዩ ድጋፍ የአርብቶ አደሩን መሰረታዊ ፍላጎት ያሟላ መሆኑን በተመለከተ፡-

- በየወረዳዎቹ የልማት ሰራተኞች የሚመደቡ በመሆኑ ከዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች(የዳልጋ ከብቶች ብዛትን የመኖ አቅርቦት በቶን /ኪ.ግ/፣ የተሰጡት የስልጠና አይነትና የሰልጣኞች ዝርዝር፣ የውሃ ኩሬዎች ብዛት፣ የባለሙያ ስም ዝርዝር፣ የዳልጋ ከብት የሞት መጠንና በምን እንደሞቱ የሚያሳይ መረጃ) በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል በዚህ መልኩ የሚሰበሰብበትና የሚጠናቀርበት ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

- አርብቶ አደሩ፣ የልማት ሰራተኞችና ባለሙያዎች ከዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ጋር በተያያዘ (በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ጤና አጠባበቅ፣ በግጦሽ መሬት አስተዳደር፣ በሰው ሰራሽ የማዳቀል አገልግሎት እና ሌሎች የዳልጋ ከብትን ምርትና ምርታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ) ወቅታዊ የሆኑ ሥልጠናዎች ቢሰጡ እና ስለ ተግባራዊነቱም ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ቢዘረጋ ዘርፉን ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል፡፡

- ለአርብቶ አደሩ በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዙሪያ የሚደረገው ልዩ ድጋፍ በመኖና በውሃ አቅርቦት እና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ላይ በስፋት ቢሰራ የአርብቶ አደሩ አቅም ክፍተት ሊሟላ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ከዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚገኘውን ሀብት አርብቶ አደሩም ሆነ ሀገሪቷ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላትን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ሚኒስቴር መ/ቤቱን የማይመለከቱ ቢኖሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፤ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የአርብቶአደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት፣ የኦሮሚያ አርብቶ አደር ኮሚሽን፣ የግብርና ሚኒስቴር እና የክልል መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡